# ሕወሓትና ፒራና

ግርማ በላይ

በትግርኛ «ጠዓመኒ ድግመኒ» የሚባል አነጋገር እንዳለ አውቃለሁ:: በአማርኛም «ጣመኝ ድገመኝ» የሚል አይኖርም ብዬ አላስብም:: ባለፈው ከኢትዮሚዲያ የአንድ ሰው ጽሑፍ ተነስቼ ስለወያኔ ዛፍ የሞነጫጨርኩዋት ወረቀት በሰደድኩዋት አብዛኛው ቦታ ስላየሁዋት ብርታት ሰጠችኝና አሁንም ኪቦርዴን አነሳሁ - ብዕር እየቀረ አይደል? ስንት ዘመን ለፍቶ ሲያበቃ ኪስ ማሞቂያ ሆኖ መቅረቱ ግን ትንሽ ቅር ማሰኘቱ አይቀርም::

የዛሬው መነሻየ ደግሞ አሁን በኢትዮላዮን ድረ ገጽ ላይ ያነበብኩት ከካናዳ የተላከ አጭር ጦማር ነው - የዚያኔውም የአሁኑም መነሻየ አጫጭር መሆናቸው የኔንም ሃሳብ እያሳጠሩት እንደሆነ ይገባኛል:: «የነገር ወጡ መጣፈጡ» እንጂ መግተልተሉ ስላይደለ እጥን ምጥን ግን ደግሞ ኩርጥ ያለች ነገር ማቅረብ ከተቻለ ውብ ነው እንጂ መጥፎ አይመስለኝም:: ማንበቢያ ጊዜም እያጠጠን መጥቷል:: ጊዜው እኮ ጠቅሎ የሩጫ ሆነ ኝ ሩጫው እንደነ ኃይሌና ደራርቱ ሞቅ ያለ ገንዘብ ቢያስገኝ እሰየው ነበር:: የብዙዎቻችን ሩጫ ግን በአትሌቲክሱ መንድር ያሯሯጭን ያህል እንኩዋን ዋጋ አላስገኛ እያለ ተቸገርን:: ብቻ ይሁን ግዴለም ደጉን ዘመን ያምጣ ብሎ መጸለይ ነው::

*«ሕጋዊ ማህበራችንን ለማዳን ስንጮህ ድምጻችንን ነጥቀው ተመሳሳይ የሀሰት ጩኸት በማሰማት ግራ እንዳያጋቡን ብልህና አስተዋይ መሆን አለብን። ማህበሩን አፍርሰው በየአካባቢው የጎሳ ማህበራትን ለማቋቋም እየሰሩ መሆኑንም የአአደባባይ ምስጢር ነው። በመሀከላችንም ንፋስ እንዳይገባ መጠበቅና መከላከልም አለብን።*

*የኢትዮጵያን ማህበርንና ተቋማትን ከወያኔ ሰርጎ ገቦች እንጠብቅ!»*

ሰሞኑን ባነበብኩት አንድ ረዘም ያለ የእንግሊዝኛ መጣጥፍ ላይ እንደተረዳሁት ደግሞ የወያኔው መንግሥት ተፅዕናና ብትር በሀገር ወስጥ ብቻ ተውስኖ የቀረ ሳይሆን በመላው ዓለም ላይ ተሠማርቶ ጥቅሞቹንና ፍላጎቶቹን በማንኛውም መንገድ - ከድሃው የኢትዮጵያ ሕዝብ በግብርና በቀረጥ እንዲሁም በአንድ አዳር ሳይቀር ተቀርፀው በሚያድሩ የወሮበላ ሕገ ወጥ ሕጎች አማካኝነት በዝርፊያ የሚያግበሰብሰውን ገንዘብ በዋነኛነት ጨምሮ - ባመቸው ዘዴ ሁሉ የሥርዓቱን ዕድሜ በማራዘም ሥራ ላይ እንደተወጠረ ይነገራል:: ይህ የአጥፍቶ ጠፊን ሥልት የኮረጀ የሚመስል አካሄድ እስከምን ድረስ ሊያዛልቀው እንደሚችል ገና የምናየው መሆኑ እንዳለ ሆኖ ሁኔታው ግን ለጊዜው እጅግ አደገኛ መሆኑ ግልጽ ነው:: አበው ሲተርቱ « አንበሣን ፈርቼ ዛፍ ላይ ብወጣ ነብር ጠበቀኝ» ይላሉ የዚህ ዓይነት መሄጃ የሚያሳጣ ድቅድቅ ጨለማ ሲገጥማቸው:: እግዚሃር ያሳያችሁ፤ ክርስቶስ ያመላክታችሁና አንድ ሰው በሀገሩ ሳይመቸው ቀርቶ «ይስፋችሁ፤የኔንም ድርሻ ሳልወድ በግዴ እንደወሰዳችሁትና እንዳስራባችሁኝ ጠቅልዬ ልሰደድላችሁና በሁሉም ነገር ላይ ብቻችሁን ተንቦራቦሩበት . . .» ብሎ በተሰደደ ዜጋ ላይ አላስካና ሳይቤሪያ፤ሆኖሉሉና ቲምቡክቱ ድረስ እየሄዱ በሰውም ሀገር ጣልቃ እየገቡ በምድር ላይ አላስኖር ማለት ምን ይባላል? ይህን አረመኔያዊ ተግባርስ ፈጣሪ ይወደዋል ወይ? እሺ የፈጣሪን መንገድስ አያውቁትም እንበል - በርግጥም አያውቁትምና - ከሌሎች እንስሳት የሚለያቸው አንጎል (ኅሊና) ምን ይላቸዋል? ዳሩ እሱም ላይኖራቸው ይችላል:: የገንዘብና የሥልጣን እንጂ የጤናማ ኅሊና ባለቤቶች ቢሆኑማ ኖሮ ዕድለኞች በሆንን ነበር:: ግን ግን ማታ ሲተኙ ድንገት መጥቶ «አሁን እንዲያው በውነቱ ስታደርጉት የዋላችሁት ክፋት ከሰው ጋር ያናኑራችኋል? በዚህ ዕኩይ ምግባራችሁስ ልጅ/ዘር ይወጣልናል ብላችሁ ታስባላችሁ?» አይላቸውም ይሆን?

እነሱ ልጅ ይውጣላቸው አይውጣላቸው የራሳቸው ጉዳይ:: በሰው ነገር ላያገባኝ ገብቼ የተነሳሁበትን ዘነጋሁ መሰለኝ:: እኔ ለራሴ የምገኝ ኢትዮጵያ ውስጥ የቶሮንቶዎች ችግር ለኔ ምኔ ሆነና ልጨነቅበት? ራሳችሁ መፍትሔውን ፈልጉና «አናስገባም ወያኔን እደጅ ይተኛ» በሉ እዚያው፤ ውስጣችሁን በጥንቃቄ ፈትሹና አጭበርባሪና ምንደኛ የወያኔ ቅጥረኛን መንጥራችሁ ተቋሞቻችሁንና ብቸኛ ተስፋዎቻችሁን ጠብቁ - ሀገር እስኪኖራችሁና እስክትሰባሰቡ ማለት ነው:: በዚያ ላይ በሀገር ቤት ላለው በሚሊዮኖች ለሚቆጥር ሕዝብ የኑሮ ተስፋና የወደፊት የሀገር ግንባታ ዋነኛ ምሰሶ መሆናችሁን ለአፍታም መዘንጋት የለባችሁም:: በትምህርቱም በሳይንሱም ኢትዮጵያ አንጋጣ በተስፋ የምትጠብቀው እንናንት በውጭ ያላችሁትን ልጆቹዋን ነው:: እኛማ ከሞትን ሰነበትን:: የሚያስቀይም ነገር ቀርቶ የሚያስደስት ነገር እንኩዋን መናገር የማይፈቀድልን ግዑዛንና ድንዙዛን አድርገውን በነፍስ በሥጋችን እየተጫወቱብን ናቸው:: ብንስቅ አያምርብን፤ ብናኮርፍ የሚያላግጥብንና የሚያሾፍብን እንጂ ብሶታችንን የሚያዳምጥ የለን:: በቃ - ደምበኛ ተንቀሳቃሽ ድንጋዮችና ሬሳዎች አድርገውናል:: እንደአሻንጉሊቶቻቸው ቢቆጥሩንም

ሲያንሰን ነው፤ ባንድ በኩልም ዕድለኝነት ነው። በበኩሌ ያንጉሊቶቻቸውን ያህል ብቆጠር ደስታውን አልችለውም። ከኛ ይልቅ ለነሱ ያላቸው ውዴታና ፍቅር ለዬት ስለሚል ነው ይህን አይመኙት ነገር መመኘት የበቃሁት። 80 ሚሊዮንን ሕዝብ እንዲህ ቀፍድዶ መያዝ ለካንስ እንዲህ ቀላል ኖሯል እናንተዬ! የገሪክና የጣሊያን መንግሥቶች አቶ መለስን ለአንድ ወር ተውሰው ሕዝባቸውን ፀጥ የማያደርጉ ለምን ነው ታዲያ? ቂሎች መሆን አለባቸው! ገና ከአውሮፕላን ሲወርድ ነበር ሁሉዋም በየጎሬዋ የምትደበቅ መምር ነጭ ሁላ!

በመቶዎች ምናልባትም በብዙ ሽዎች ከሚቆጠሩ የአሣ ዝርያዎች መካከል ፒራና(piranha) አንደኛዋ ናት። ታሪኩዋን ብትከታተሉ እንዲህ ቀላል እንዳትመስላችሁ። በመጠን ከብዙዎቹ የአሣ ዝርያዎች ያነሰች ትሁን እንጂ የተፈጥሮ ግዳጅዋን ‘አድምታ’ በመሥራት የሚስተካከላት አሣ የለም - አስፈሪው ሻርክም እንኳን ቢሆን አይደርስባትም። ያ ሥራዋ ደግሞ ግዳይዋን በሩቅ ለመለየት ተፈጥሮ የሰጣትን ልዩ የማነጣጠር ችሎታ ተጠቅማ በብርሃን ፍጥነት ዒላማዋ ላይ በመድረስ በሴከንዶች ውስጥ የዶጋ አመድ ማድረግ ነው። ባጠመዱት ዘንቢልና ሳህን ውስጥ ይቺን አሣ ከነነፍስዋ ያገኙ ስንትና ስንት አሣ አጥማጆች ጉድ ሆነዋል መሰላችሁ - ባሕርይዋን ሳይረዱ በጃቸው ለቀም ሲያደርጓት እስኪለቁዋት እጃቸውን በሞረድ ጥርሶችዋ በቅጽበት ላፍ ታደርጋቸዋለች፤ ባይገርማችሁ በዚህ ዓይነቱ መጥፎ አጋጣሚ መላ አፉን ያጣ አለ አሉ - ስስታም አንድ ያንቀው አንድ ይወድቀው አይደል ተረቱስ? ለጠቅላላ ዕውቀታችን ያህል እንጂ ወያኔ እንኩዋን የፒራናን ያህል አይደለም የዓሣማን ያህልም ሆዳም አይደለችም፤ በጭራሽ፤ ምን በወጣት! ለምናልባቹ - gb5214@gmail.com